# ክሩን ለመበጠስ

ዮናስ 05-30-18

ከ (2008-2012) የተያዘው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ሁሉን-አቀፍ ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት በማስቀጠል የሀገራችንን የህዳሴ ጎዞ ከማሳካት፣ የኢኮኖሚ መሠረተ-ልማቶችንና ማህበራዊ አገልግሎቶችን ለዜጎች በፍጥነትና በጥራት ተደራሽ ከማድረግ፣ የሥራ ስምሪትን በማሳደግ ድህነትን ትርጉም ባለው ሁኔታ ከመቀነስና በሂደትም ከማስወገድ እና የዜጎችን የኑሮ ደረጃ ከማሻሻል አንፃር ቁልፍ ስትራቴጂ መሆኑ ላይ ሃገራዊ መግባባት ተይዟል፡፡

በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ አጠቃላይ ኢኮኖሚው በ2017 ኢትዮጵያን ዝቅተኛ መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሃገሮች ተርታ ለማሰለፍ የተቀመጠውን ሃገራዊ ራዕይ ሊያሳካ በሚያስችል ፍጥነት ግን አልተጓዘም፡፡ የኢኮኖሚ ዕድገቱ ፈጣን ብቻ ሳይሆን ቀጣይና ሁሉን አቀፍ እንዲሆን የታሰበው ከዚህ በላይ በሆነ ፍጥነት መጓዝን ታሳቢ አድርጎ ነው፡፡ ይህ ባለመሆኑም ያሳለፍናቸውን ሶስት አመታት የሃገሪቱ ዜጎች በየደረጃው በሚካሄዱ የልማት ሥራዎች ዕኩል ተሳታፊና ፍትሀዊ ተጠቃሚ መሆን ባለመቻላቸው ለሌላና ተጨማሪ ጥፋት ተጋልጠን ሰንብተናል።

የሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዋነኛ ዓላማ እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር በ2017 ሀገራችንን ዝቅተኛ መካከለኛ ገቢ (Lower Middle Income) ካላቸው ሀገሮች ተርታ ማሰለፍ ነው።ስለሆነም በተለይ ለማኑፋክቸሪንግ ፈጣን ዕድገት ብሎም የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ሽግግር ዕውን ለማድረግ የተደራጀና የተቀናጀ እንቅስቃሴ የሚደረግ ስለመሆኑ በእቅዱ ተመልክቷል፡፡

የኢኮኖሚ ዕድገቱ እንዳለፉት ዓመታት ሁሉ መሠረተ ሰፊ እና በዋናነት ግብርና የዕድገቱ ዋና ምንጭ ሆኖ ኢንዱስትሪ በላቀ ፍጥነት የሚያድግበትና፣ የአገልግሎት ዘርፍ የበኩሉን ሚና የሚጫወትበት የሚሆን መሆኑም በተመሳሳይ፡፡

በዚህ መሠረት በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን ኢኮኖሚው በአማካይ በየአመቱ በ11 በመቶ እንደሚያድግ ትንበያው ያመለክታል፡፡ ይህ ስትራተጂክ ግብ ሊደረስበት እንደሚችል

ያለፉት ዓመታት አፈፃፀሞች መነሻ የተደረጉ መሆኑም በእቅዱ የተመለከተ ቢሆንም የብሄራዊ ፕላኒንግ ኮምሽን የሁለት አመታት ተኩል ግምገማ ግን በዚህ ልክ አለመፈጸሙን ያሳያል፡፡

ኢትዮጵያ ከ2003 እስከ 2007 የተገበረችውን የመጀመሪያው የዕድገትና ትራንስፎ ርሜሽን እቅድ በድል በፈተናም አጠናቃለች። ከላይ በተመለከተው አግባብ የዚህ እቅድ ዋና ግብ በኢትዮጵያ አቆጣጠር በ2017 አገሪቱን ዝቅተኛ መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገሮች ተርታ ማሰለፍና ለዚህ የሚመጥን አጠቃላይ አገራዊ አቅም መገንባት ነው፡፡የማክሮ ኢኮኖሚ ዋና የፖሊሲ ግቦችም ይህንኑ ራዕይ ከማሳካት አንፃር የተቃኙ ናቸው፡፡ በተለይም በአገሮች ተሞክሮ ለስኬታማ የኢኮኖሚ ትራንስፎ ርሜሽን ቁልፍ አመልካች እንደሆኑ የሚታመ ንባቸው ሦስት መሠረታዊ የማክሮ ኢኮኖሚ ክስተቶች ማለትም ከፍተኛ የኢኮኖሚ ዕድገት፣ የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥና፣ ከፍተኛ የካፒታል ክምችት ምጣኔ የማክሮ ኢኮኖሚ ዋና ግቦች ናቸው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የተሳካ የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥ ለማምጣት የተረጋጋ የማክሮ ኢኮኖሚ መኖር ወሳኝ በመሆኑ ይህንንም ማረጋገጥ የዕቅዱ አንዱ ግብ ነው፡፡ ሰሞኑንም ብሄራዊ ፕላን ኮሚሽን የሁለት አመታት ተኩሉን የእቅድ አፈጻጸም ይፋ አድርጓል።

በሁለተኛው የእድገትና ትርንስፎርሜሽን እቅድ የኢኮኖሚውን የዕድገት አቅጣጫ በአምራች ዘርፎች በተለይም በአምራች ኢንዱስትሪው እንዲመራ አቅጣጫ ተቀምጧል፡፡ እነዚህንና ሌሎች ተጓዳኝ ግቦችን ለማሳካት የተረጋጋ የማክሮ ኢኮኖሚ የማረጋገጥና ዋና ዋና ግቦቹን የመደገፍ ዓላማ ያላቸው የማክሮ ኢኮኖሚ ፖሊሲ ግቦችም ተቀምጠዋል፡፡ በአጠቃላይ በዕቅድ ዘመኑ በመሠረታዊ የዕድገት አማራጭ የ11 በመቶ እና በከፍተኛው የዕድገት አማራጭ የ12 ነጥብ 3 በመቶ አማካይ አገራዊ የምርት ዕድገት፣ የ29 ነጥብ 6 በመቶ አገራዊ የቁጠባ ምጣኔ፣ የ41 ነጥብ 3 በመቶ የኢንቨስትመንት ምጣኔ፣ መዋቅራዊ ለውጥና የተረጋጋ የማክሮ ኢኮኖሚ ሁኔታን ማስፈን ዋና ዋናዎቹ የሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎ ርሜሽን ዕቅድ የማክሮ ኢኮኖሚ ግቦች ናቸው፡፡

ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት በመነጨበት ክፍለ ኢኮኖሚ የ11 ነጥብ 2 በመቶ ዕድገት እንደሚያስመዘግብ ግብ ተቀምጦ የነበር ቢሆንም፤ በኤልኒኖ ክስተት በተፈጠረው ድርቅ ሳቢያ እና በግጭቶች መፈተኑ ለበጀት ዓመቱ ከተቀመጠው የ11 ነጥብ 2 በመቶ ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ዕድገት ግብ የ3 ነጥብ 2 መቶኛ ነጥብ ቅናሽ በማሳየት ኢኮኖሚው በ8 በመቶ ብቻ አድጓል፡፡ በተለይም በበጀት ዓመቱ

ለኢኮኖሚው የ36 ነጥብ 7 በመቶ ድርሻ ያለው የግብርናው ክፍለ- ኢኮኖሚ የ8 ነጥብ 2 በመቶ ዕድገት ምጣኔ ያመጣል ተብሎ በእቅድ ቢያዝም፤ በ2.3 በመቶ ብቻ ሊያድግ ችሏል። በዚህም ምክንያት ለአጠቃላይ የአገር ውስጥ ምርት ዕድገት ከዕቅድ በታች መሆን ከፍተኛ ተጽዕኖ አሳድሯል፡፡

በአንጻሩ በበጀት ዓመቱ የኢንዱስትሪው ዘርፍ የ20 ነጥብ 6 በመቶ እና የአገልግሎት ዘርፍ የ8 ነጥብ 7 በመቶ ዕድገት በማስመዝገብ በአጠቃላይ ለተመዘገበው የ8 በመቶ የኢኮኖሚ ዕድገት ትልቅ አስተዋጽኦ ነበራቸው፡፡ በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን አገራዊ ቁጠባንና ኢንቨስትመንትን በማሳደግ የፈጣን ዕድገቱ ምንጭ እንዲሆኑ የማስቻል ግብ ተቀምጧል። በዚህም መሠረት በኢኮኖሚው ውስጥ የተደረገው የኢንቨስትመንት መጠን ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ያለው ድርሻ 38 ነጥብ 5 በመቶ ሆኖ ተመዝግቧል። ይህም ከተተነበየው የ37 ነጥብ 7 በመቶ ምጣኔ ጋር ሲነጻጸር የ1 ነጥብ 2 በመቶ ጭማሪ አሳይቷል፡ ፡ በተመሳሳይ ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ቁጠባ ምጣኔ በ2007 በጀት ዓመት ከነበረበት የ21 ነጥብ 9 በመቶ ወደ 22 ነጥብ 4 በመቶ ከፍ ብሏል፡፡

በእቅድ ዘመኑ የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥ ከማምጣት አንጻር ከታቀደውና ከተጠበቀው አንፃር የተመዘገበው የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ሽግግር ዝቅተኛ ቢሆንም ከግብርና ዘርፍ ወደ ዘመናዊ የኢኮኖሚ ዘርፎች (ኢንዱስትሪና አገልግሎት) የመዋቅራዊ ሽግግር ታይቷል፡ ፡ ከኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥ አንፃር ትልቅ ትኩረትና ትርጉም ተሰጥቶት የነበረው የማኑፋ ክቸሪንግ ኢንዱስትሪ በ18 ነጥብ 4 በመቶ በማደግ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ያለውን ድርሻ ለመጀመሪያ ጊዜ 5 ነጥበ 4 በመቶ ሆኖ ተመዝግቧል፡፡ በአንጻሩ የሀገሪቷ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ያለው ድርሻ ከሰሃራ በታች ካሉ የአፍሪካ አገራትም ሆነ በዝቅተኛ የዕድገት ደረጃ ላይ ከሚገኙ የዓለም ሀገራት አማካይ አፈጻጸም ጋር ሲነፃፀር ግማሽ ያህል ነው፡፡

በተመሳሳይ የሸቀጦች የወጪ ንግድ ገቢ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ያለውን ድርሻ በማሳደግ እና የኢኮኖሚ ዘርፎችን የሥራ ስምሪት ስብጥር ዝቅተኛ ምርታማነት ካላቸው የኢኮኖሚ ዘርፎች ከፍተኛ ምርታማነት ወዳላቸው ዘርፎች በማሸጋገር የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥን ለማፋጠን የታቀደውን ግብ ከማሳካት አኳያ ዝቅተኛ አፈጻጸም እንደሆነ መረጃው ያሳያል፡፡ ይህም ከግብርና ዘርፍ ወደ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ዘርፍ የሚደረገውን የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥ ለማፋጠን የተቀመጠውን ሀገራዊ ራዕይና ግብ ለማሳካት በቀጣይ ከፍተኛ ጥረት ማድረግ እንደሚገባ ያመለክታል፡፡

በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን ከተያዙት የማክሮ ኢኮኖሚ ግቦች መካከል አንዱ የተረጋጋ የማክሮ ኢኮኖሚ እንዲኖር ማስቻል ነው፡ ፡ ለዚህም ተግባራዊ የተደረጉ የኢኮኖሚ መዋቅራዊ አቅጣጫዎች፣ የፊስካልና የገንዘብ ፖሊሲዎች እንዲሁም አስተዳደራዊ ዕርምጃዎች የተረጋጋ የማክሮ ኢኮኖሚ ሁኔታን ለማረጋገጥ ያለሙ ናቸው፡፡ በዚህም በገንዘብና በፊስካል ፖሊሲዎች በኩል የተሻለ አፈጻጸም ታይቷል፡ ፡ የመሠረተ-ገንዘብ (base money) ዕድገትን በመቆጣጠር እና ጥብቅ የፊስካል ፖሊሲ በመከተል በድርቁ ምክንያት ከተፈጠረው የአቅርቦት እጥረት ሥጋት ጋር ተያይዞ ሊከሰት ይችል የነበረውን ከፍተኛ ዓመታዊ አማካይ የዋጋ ንረት በሰኔ ወር መጨረሻ በ9 ነጥብ 7 በመቶ መገደብ ተችሏል፡፡

ይህም የሚያመለክተው መንግሥት የሚከተ ላቸው ጥብቅ የገንዘብና የፊስካል ፖሊሲዎች የተፈለገውን ውጤት እያሳዩ መሆናቸውን ነው፡፡ በተጨማሪም በዓለም አቀፍ ደረጃ የአንዳንድ ሸቀጦች (የነዳጅ) ዋጋ መቀነስ እንዲሁም በአንዳንድ አካባቢዎች የተከሰተው ኤልኒኖ አመጣሽ ድርቅ የዋጋ መረጋጋቱ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ እንዳያስከትል መንግሥት ጥብቅ የገንዘብና የፊስካል ፖሊሲዎች መከተሉ እንዲሁም ከፍተኛ መጠን ያለው ስንዴ ከውጭ ማስገባቱ በሰኔ ወር መጨረሻ ለተመዘገበው አጠቃላይ አገራዊ የዋጋ ግሽበት በነጠላ አሃዝ እንዲገደብ አስተዋፅኦ አድርገዋል።

የሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የፊስካል ፖሊሲ በዋነኛነት በተግባር ላይ ያሉትን የታክስ ፖሊሲዎች በውጤታማነት በማስተዳደር የታክስ ገቢን ማሳደግ እና የወጪ አመዳደብ በካፒታል ኢንቨስትመንት እና ድህነትን በመዋጋት ረገድ ቁልፍ በሆኑ ዘርፎች ላይ እንዲያተኩር ማድረግን ያለመ ነው፡ ፡ በዚህም መሠረት የታክስ ገቢ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ያለው ድርሻ (Tax to GDP Ratio) በ2007 ከነበረበት የ12 ነጥብ 7 በመቶ ምጣኔ የ0 ነጥብ 2 መቶኛ ነጥብ ቅናሽ በማሳየት ወደ 12 ነጥብ 5 በመቶ ዝቅ ብሏል፡፡ እንዲሁም በዕቅድ ከተያዘው የ13 ነጥብ 7 በመቶ ምጣኔ አንፃር ሲታይም የ1 ነጥብ 2 መቶኛ ነጥብ ጉድለት እንዳለው መረጃው ያሳያል፡፡ይህ አፈፃፀም ከፍ ያለ ጉድለት የታየበት እና ካለፉት ዓመታት አማካይ አፈጻጸሞችም ዝቅ ያለ በመሆኑ በቀጣይ የላቀ የፖለቲካ አመራር ትኩረትን ይፈልጋል።

የወጪ ንግዱ እንደመጀመሪያው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን ሁሉ በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመንም ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶታል፡ ፡ ይህ ዘርፍ ለአምራች ኢንዱስትሪ

ምርቶች ተወዳዳሪነት መጨመር ከሚኖረው ሚና በላይ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪን በማስገኘት የመዋቅራዊ ለውጥ ሽግግሩን መደገፍ ይጠበቅበታል፡ ፡ ሆኖም እሥካሁን ከጠቅላላ የሸቀጦች ወጪ ንግድ የተገኘው የውጭ ምንዛሪ ገቢ 2 ነጥብ 9 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር ብቻ ሆኖ ተመዝግቧል፡ ፡ በአጠቃላይ ጠቅላላ የሸቀጦች ወጪ ንግድ መጠን (Volume) በ7 ነጥብ 2 በመቶ የጨመረ ቢሆንም፤ የሸቀጦች ወጪ ንግድ አማካይ ዓለም አቀፍ ዋጋ በ11 ነጥብ 1 በመቶ ቀንሷል። በዚህም ከዘርፉ የተገኘው የውጭ ምንዛሪ ገቢ ከ2007 በጀት ዓመት አፈፃፀም ጋር ሲነፃፀር በ5 በመቶ ገደማ ቀንሶ ታይቷል፡ ፡ ይህ ደካማ አፈጻጸም በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎ ርሜሽን ዕቅድ ዘመን መጨረሻ (በ2012 በጀት ዓመት) ከሸቀጦች የወጪ ንግድ ለማግኘት የታቀደውን የ13 ነጥብ 9 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር ገቢ ዕቅድ ለማሳካትና የታቀደውን የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥ ለማረጋገጥ እስከአሁን ከተደረገው የተሻለ ጥረትና ርብርብ እንደሚያስፈልግ ያመላከተ ነው፡ ፡

የተቋማት ብቃትና ለውጥ ለትራንስፎርሜሽኑ ስኬት ወሳኝ ነው።የኢትዮጵያ የኢኮኖሚ ፖሊሲዎች በተሞክሮ እየዳበሩ በረጅም ጊዜ ሂደት በትክክለኛ አቅጣጫ ላይ ስለመሆናቸው ብዙም የሚያከራክር ጉዳይ የለም። ነገር ግን የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥ ወደ አዳዲስ አሠራሮች ስለሚያመራ ይህን አዲስ አሠራርና የኢኮኖሚ መጠን ማሳለጥ የሚችል ተቋማዊ ብቃት ይጠይቃል፡ ፡ በመሆኑም ቀጣይ ግምገማዎች የተቋማት አፈጻጸም ላይ ጭምር ያተኮሩ እንዲሆኑ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ለመልካም ውጤት የታሰቡ የኢኮኖሚ ፖሊሲዎች የተዋኒያንን ባሕርይ በመቀየር ላልተፈለገ ውጤት ሊዳርጉ ይችላሉ ለምሳሌ ዕቃዎችን ከቀረጥ ነፃ የማስገባት መልካም ፖሊሲ እያጋጠመው ያለውን የኪራይ ሰብሳቢነት ፈተና ማስተዋል ይቻላል ስለሆነም ከኢኮኖሚ ፖሊሲዎች ጎን ለጎን የማበረታቻና የእርምት ስልቶችን የያዙ ነገር ግን በእርግጠኝነት የሚተገበሩ ማዕቀፎችን መጠቀም  ክሩን በአሸናፊነት ለመበጠ  ስ ያስችላል።

ይህም ሆኖ በግልጽ መታወቅ ያለበት ጉዳይ የተቀመጠው አማካይ ዓመታዊ ዕድገት ከፍተኛ ጥረት የሚጠይቅና ከዓመት ወደ ዓመት እየከበደና እየተወሳሰበ የሚሄድ መሆኑን ነው፡፡ በአጠቃላይ በሁሉም የኢኮኖሚ ዕድገት ምንጮች የሥራ ሥምሪትን በማሳደግ፣ ምርታማነትን በማሻሻል፣ ጥራትንና ተወዳዳሪነትን በማረጋገጥ በኢኮኖሚው ውስጥ የሚጠበቀውን የመዋቅር ለውጥ ለማምጣት ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶ የሚሠራ ሲሆን ይህንኑ ለማረጋገጥ በዘርፎች መካከል ጠንካራ ትስስር እና ተመጋጋቢነት እንዲፈጠር ማድረግ ክሩን በአሸናፊነት ለመበጠስ ያስችላል፡፡

የሚጠበቀው ፈጣንና ቀጣይ የኢኮኖሚ ዕድገት ሰፊ የሥራ ዕድል እንዲፈጠር የሚያስችል መሆን አለበት፡፡ ከዚህ አኳያ የማኑፋክቸሪንግን መሠረት የሚያሰፉ የጥቃቅን፣ አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች በከፍተኛ ፍጥነት እንዲበራከቱና ትላልቅ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎችም ጉልበትን በስፋት የሚጠቀሙ ሆነው ሰፊ የሥራ ዕድል እንዲፈጥሩ ለማድረግ በሚያስችል ቅኝት ሩጫው ሊከናወን ይገባል፡፡

የኢኮኖሚው የማምረት አቅም ላይ ለመድረስ ቅልጥፍና መጨመርና አምራች ዘርፎችን በማጐልበት በጥራት፣ በምርታማነትና በተወዳዳሪነት የላቀ ዕድገት ማምጣት፣ የሀገራችን ኢኮኖሚ አሁን ባለበት ደረጃ የማምረት አቅሙ ላይ ለመድረስ ገና ከፍተኛ ቅልጥፍና መጨመር እንዳለብን የሚያመላክት አፈጻጸም ነው የተመለከትነው፡፡

አምራች ዘርፍ የምንላቸው የግብርና የተለያዩ ንዑስ ዘርፎችና ከኢንዱስትሪም የተለያዩ የማኑፋክቸሪንግ ንዑስ ዘርፎች ናቸው፡፡ ከግብርና አኳያ ሲታይ የዕድገቱ ምንጭ በአነስተኛ አርሶ አደሮችና አርብቶ አደሮች ቤተሰቦች በሚካሄድ ልማት ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ በእጃችን ያሉ ቴክኖሎጅዎችን በአግባቡ አባዝተን ብናሰራጭና የኤክስቴሽን ሥርዓቱን ባስቀመጥነው አቅጣጫ መሠረት ተግባራዊ ብናደርግ ማለትም የማስፋት ስትራተጅያችንን በልማት ሠራዊት አማካይነት ብንፈፅም እጅግ የላቀ የምርታማነትና የምርት መጠን መድረስ የሚያስችለን ይሆናል፡፡ ስለሆነም ከግብርና አኳያ በሰብል ልማትም ሆነ በእንስሳት ሀብት ልማት እንዲሁም የተፈጥሮ ሃብት ልማትና የመስኖ ሥራን ጨምሮ የማምረት አቅማቸው ድረስ እንዳንደርስ ያገዱንን ማነቆዎች መፍታት ወይም ቅልጥፍናን ማሻሻል የሩጫው ዋነኛ አቅጣጫ ሊሆን ይገባዋል፡፡ በአሸናፊነት ክሩን ለመበጠስ ከዚህ በተጓዳኝ አሁን ባለው ቴክኖሎጅ የማምረት አቅማቸው ደረጃ ለተቃረቡ ሞዴሎች ተጨማሪ አዳዲስ ቴክኖሎጅዎችን የማዘጋጀት የማባዛትና የማሰራጨት ሥራ በተጨማሪነት መሠራት ያለበት ይሆናል፡፡ ከስትራቴጂክ የምግብ ሰብሎች ምርታማነት መሥመር በተጓዳኝ ልዩ ትኩረት ተሰጥቶ የማምረት አቅማችንን ማሻሻል ያለብን በሆርቲካልቸርና በእንስሳት ሀብት ልማት እንዲሁም ሌሎች የኢንዱስትሪ ግብዓቶችና የኤክስፖርት ምርቶች ላይ ማድረግም ሌላኛውና ክሩን በአሸናፊነት ለመበጠሥ የሚያስችል አቅጣጫ ነው፡፡